የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ኢትዮጵያ

ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባ - 1996/97 በዲሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብቶችና ሠራተኛ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ የካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም

ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አመራር ፣ ከአሃዳዊ ወደ ፌደራላዊ ሥርዓተ መንግሥት መሸጋገሯን ቀጥላለች ። ዓለም አቀፋዊ እና የአገር ውስጥ ታዛቢዎች በመሰከሩት መሰረት 1992 ዓ.ም. የተደረጉት ብሔራዊ ምርጫዎች በአብዛኛው አካባቢዎች ነፃ እና ትክክለኛ ነበሩ። ሆኖም በደቡብ ክልል፣ በተለይም በሀዲያ አካባቢ ፣ አሳሳቢ እና ሕገ ወጥ የሆኑ የምርጫ አሰራሮች ተፈጽመዋል። በዚሁ ዓመት በተደረገው መርጫ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) እና ተባባሪዎቹ ፓርቲዎች 548 መቀመጫዎች ካሉት በፌደራሉ ምክር ቤት ውስጥ 519ኙን ይዘዋል። እንደዚሁም ኢሕአዴግ እና ተባባሪዎቹ ፓርቲዎች ሁሉንም የክልል ምክር ቤቶች በከፍተኛ አብላጫነት ይዘዋል። እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የአዲስ አበባ ክልል ምክር ቤት እንደፈረሰ የቆየ ሲሆን ፣ ከግንቦት ወር 1997 ዓ.ም. በፊት አዲስ ምርጫዎች ይደረጋሉ ተብሎም አይጠበቅም ። የፖለቲካ ፓርቲዎች በአመዛኙ በነፃነት ላይ የተመሠረቱ ቢሆንም፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቀስ በቀስ በመጠናከር ሂደት ላይ ነበሩ። በታህሣሥ ወር 1995 ዓ.ም. ስምንት የመንግሥት ሠራተኞች ማንነታቸው ባልታወቀ አጥቂዎች ከተገደሉ እና በዚሁም የተነሳ ጥቂት የሠራዊቱን እና የፖሊስ አባላትን ጨምሮ የአካባቢው ወሮበሎች በአኙዋክ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የበቀል ግድያዎች ከፈጸሙ በኋላ ፣ በዓመቱ ውስጥ በጋምቤላ የነሳ ግጭት ቀጥሏል። የፍትሕ ሥርዓቱ ደካማ እና የሥራው ብዛት የተጫነው ቢሆንም፣ በነፃ የመሥራት ምልክቶችን ማሳየቱን ቀጥሏል። የተከማቹ ጉዳዮችን እያዩ በመቀነስ ረገድ እመርታ ተደርጓል። የአካባቢ አስተዳደራዊ ፣ የፖሊስ እና የፍትሕ ሥርዓቶች በመላ አገሪቱ ውስጥ ደካማ እንደሆኑ ቆይተዋል።

የፀጥታ ኃይሉ ሠራዊቱን፣ የፌደራል እና የአካባቢ ፖሊስን፣ እና የአካባቢ የመንግሥት ታጣቂዎችን ያካተተ ነው። ለውስጥ ፀጥታ ኃላፊነቱ በመጀመሪያ ደረጃ የፖሊስ ነው። ሆኖም ግን ከፖሊስ ዕዝ ውጭ የሆኑ የአካባቢ የመንግሥት ታጣቂዎች እንደ አካባቢ የፀጥታ ኃይሎች በመሆን ተንቀሳቅሰዋል። የመከላከያ ሠራዊት

ኃላፊነቱ ከውጭ ለሚቃጣ የፀጥታ ማናጋት ቢሆንም፣ በተለይ ከጎረቤት አገሮች ጋር ባሉት ወሰኖች አኳያ ለውስጥ ፀጥታም ጭምር አንዳንድ ኃላፊነቶች አሉበት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ተጠሪነታቸው ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ነው። ይህም በተራው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ነው። ወታደራዊ ሠራዊቱ አየር ኃይልን እና የምድር ጦርን የሚያካትት ሲሆን ፣ የዚህም ተጠሪነት ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ነው። ወታደራዊ ኃይሎች በኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ፣ መንደርደሪያው ከሶማሊያ በሆነው በአል-ኢታሃድ አል-ኢስላሚ ሽብርተኛ ድርጅት እና በአጋዴን ብሔራዊ የነፃነት ግንባር (ኦብነግ) ክፍሎች ላይ በዝቅተኛ ደረጃ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች አድርገዋል። በአጠቃላይ ሲቪል በለሥልጣኖች የፀጥታ ኃይሎችን በሙሉ የተቆጣጠሩ ቢሆንም ከፀጥታ ኃይሎች ውስጥ አንዳንድ ክፍሎች ከመንግስት ሥልጣን ውጭ በእራሳቸው የሠሩ ስለመሆኑ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ታይቷል። የፀጥታ ኃይሎች አባላት ከባድ የሰብአዊ መብቶች ረገጣዎችን ፈጽመዋል።

ኢኮኖሚው በግብርና ላይ እንደተመሰረተ ቆይቷል። 71 ሚሊዮን እንደሆነ ከሚገመተው የአገሪቱ ሕዝብ ውስጥ 85 ከመቶ የሚሆነው በዝቅተኛ ደረጃ በተመሠረተ ሁኔታ የሚኖር ሲሆን፣ የሚተዳደረውም ትናንሽ መሬቶችን ተከራይቶ በማረስ ነው። ከጠቅላላው የአገር ውስጥ ምርት ግብርና 45 ከመቶ ያህል ሸፍኗል። በዓመቱ ውስጥ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት በ6.7 ከመቶ አድጓል። የዓለም የገንዘብ ድርጅት በገለፀው መሰረት የዋጋ ግሽበት 5.5 ከመቶ እንደሆነ ተረጋግቶ ቆይቷል። በከተማዎች ውስጥ በአብዛኛው የኤኮኖሚ የሥራ እንቅስቃሴ ሲከናወን የቆየው መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ነበር። ድርቅ ፣ የሰብል መቀጨጭ ፣ እና የእንሰሳት ማለቅ 7 ሚሊዮን ያህል የሚሆኑ ሰዎችን ጎድቷል። አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት እድገትንም ጎትቶታል። የንግድ ድንጋጌዎች ተሻሽለዋል፣ ያም ሆኖ አሁንም በኢሕአዴግ ለተያዙት የንግድ ስራዎች እንዳደላ ነው። መንግሥት የአገሪቱን የፋይናንስ ይዘት ማረጋጋት የሚችል፣ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው እንዲሳተፍ የሚያደርግ ፣ እና የውጭ ኢንቨስትመንት የሚሰብ የኤኮኖሚክ ማሻሻያ ፕሮግራም በመተግበር እንደቀጠለ ቆይቷል። ሆኖም፣ ለኢንቨስትሜንት መሰናክል የሆኑ አንዳንድ ሁኔታዎች እንደነበሩ ናቸው ፤ ዝቅተኛ/አነስተኛ ጎበኝነት እንደተስፋፋ ነበር። በዓመቱ መጨረሻ (ታህሣሥ 1997) 200 ያህል የሚሆኑ መንግሥት የያዛቸው የንግድ ድርጅቶች ወደ ግል ባለቤትነት ሳይዛወሩ ይገኛሉ።

መንግሥት በሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ረገድ ያለው ሬኮርድ አሳዛኝ በሆነ ደረጃ ዘለቋል፤ አንዳንድ የተሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩም፣ ዛሬም ከባድ ችግሮች አሉ። የጸጥታ ኃይሎች የፖለቲካ ግድያን ጨምሮ ሕገ ወጥ ግድያን፣ በርካታ ታጋቾችን ደብድበዋል፣ አሰቃይተዋል፣ አንገላተዋል።

የወሕኒ ቤቶች ሁኔታ መጥፎ እንደሆነ ነው። በተለይም አነግን በመደገፍ ዝንባሌ ወይም በአባልነት በሚጠረጠሩ ላይ በማትኮር መንግሥት ከሕግ ውጭ ሰዎችን መያዝና ማገትን ቀጥሎበታል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎች ክስ ሰይመሠርትባቸው እንደታገቱ ይገኛሉ። ክስ ተመሥርቶ መታየት ከመጀመሩ በፊት ለረጅም ጊዜ ታግቶ መቆየት ችግር እንደሆነ ቀጥሏል። ዜጎች ለግላቸው ያላቸውን መብቶች መንግሥት ጥሷል፣ ለብርበራ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ስለማስፈለጉ ያለውንም ሕግ መንግሥት ብዙ ጊዜ እንደሌለ ቆጥሮታል። መንግሥት የፕሬስ ነፃነትን አጥብቧል። ቢሆንም፣ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲመዛዘን ፣መንግሥትን የሚተቹ መጣጥፎችን በመፃፋቸው ስለተያዙ፣ ስለታገቱ ወይም ስለተቀጡ ጋዜጠኞች የተዘገበው አነስተኛ ነው። ጋዜጠኞች እራስን በእራስ ሳንሱር አድርጎ መሥራትን ቀጥለውበታል። በተለይ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተመለከተ መንግሥት አንዳንድ ጊዜ የመሰብሰብ ነፃነትን ገድቧል። ሰላማዊ ሰልፍን ለመበተን የፀጥታ ኃይሎች አንዳንድ ጊዜ ከመጠን ያለፈ ኃይል ተጠቅመዋል። በማሕበር የመደራጀት መብትን መንግሥት ገድቧል። ነገር ግን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አመዘጋገብ ሂደት በመሻሻል ቀጥሏል። አንዳንድ ጊዜ የአካባቢ ባለሥልጣኖች የሃይማኖት ነፃነትን ጥሰዋል። ከአገር ለመውጣት ነዋሪዎች የመውጫ ቪዛ እንዲኖራቸው አስፈላጊ የነበረውን መንግሥት ሰርዞታል። በጎሣ ግጭቶች የተነሳ የተፈናቀሉ በርካታ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች በአገር ውስጥ እንዳሉ ናቸው። በኃይል መጠቀም፣ በሴቶች ላይ ማህበረሰብዓዊ መድልዎ ማድረግ፣ እና በሕፃናት ላይ ረገጣ መፈጸም ችግሮች መሆናቸው ቀጥሏል። ሴት ልጆችን መግረዝ የተስፋፋ ቢሆንም፣ ይህን የመሳሰሉ ሥራዎችን ለመግታት በአመራር ደረጃ የተደረጉ ጥረቶች የተወሰነ ውጤት እያስገኙ ናቸው። ለኤኮኖሚያዊ እና ወሲባዊ ዓላማዎች ሕፃናትን የመበዝበዝ ችግር እንደቀጠለ ነው። በሰዎች መነገድ ከባድ ችግር እንደሆነ ይገኛል። የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች እና በሃይማኖት እና በጎሳ ሕጻጣን የሆኑት ማኅበረሰብዓዊ መገለል ይደርስባቸዋል። በሙያ ማህበሮች፣ መንግሥት ጣልቃ መግባቱን በዝቅተኛ ደረጃ

ቀጥሏል። በተለይ መደበኛ ባልሆነ (ኢንፎርማል) የሥራ ዘርፍ ሕጻናትን አስገድዶ ማሰራትን ጨምሮ ፣ በግድ ማሠራት ችግር እንደሆነ ቀጥሏል።

ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር

ክፍል 1 - የሚከተሉትን የጨምሮ ሰውን የማይነጣጠል ወይም የዋህድነት መብት ማክበር ፤

ሀ/ ሕገ ወጥ ወይም በዘፈቀደ ሚወሰድ ሕይወትን የማሳጣት እርምጃ

በዓመቱ ውስጥ የፖለቲካ ግድያዎች የተባለቱን ጨምሮ ፣ የፀጥታ ኃይሎች በዙ ግድያዎች ፈጽመዋል። በዓመቱ ውስጥ ሕገ-ወጥ ግድያዎች ስለመፈጸማቸው ብዛት ያላቸው ዘገባዎች ነበሩ።

ተቃዋሚ የሆነው የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የመንግሥት ታጣቂዎች እና ወታደሮች ከታህሣሥ እስከ ግንቦት 1996 ዓ.ም. ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ 11 አባላቱን መግደላቸውን ዘገቧል። ለምሳሌ በመጋቢት 20 ቀን 1996 ዓ.ም. ጋሻው መሰለ እና ደሳለኝ ዳምጠው የተባሉ የመንግሥት ታጣቂዎች ደሳለኝ ስመኝ የሚባለውንና በአብነት ወረዳ ደቡብ ጎንደር አካባቢ ነዋሪ የሆነውን የመኢአድ አባል ገድለዋል። በሚያዝያ 21 ቀን የመንግሥት ታጣቂዎች የመኢአፓ የወረዳ ምክር ቤት አባል የሆነውን ኃይሉ ዘለቀን በማሼራቤል ወረዳ ገድለውታል። በግንቦት 7 ቀን የመኢአድ ወጣቶች ሊግ መሪ ጌትዬ አላጋውን የመንግሥት ታጣቂዎች በግፍ ገድለውታል። እስከ ታህሣሥ 22ቀን 1997 ዓ.ም.ድረስ በእጥፊዎቹ ላይ ምንም እርምጃ አልተወሰደም።

ተቃዋሚው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ጎብረት የወረዳው ፖሊስ አኤሊሶ ቲኤሊሶ የተባለውን ከደጋፊዎቹ አንዱ የነበረውን በሜጋቾ ቀበሌ ግቤ ወረዳ በደቡብ ክልል ምሳውን በመመገብ ላይ እንዳለ ታህሣሥ 18 ቀን 1996 ዓ.ም ተኩሶ እንደገደለው ዘግቧል። ተጠርጣሪው የፖሊስ መኮንን አልታገታም፤ ስለግድያው ምንም ምርመራ አልተደረገም።

በታህሣሥ እና ግንቦት ወራት 1996 ዓ.ም መካከል በጋምቤላ ክልል የተከሰተውን የጎሣ ግጭት እንዲመረመር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመው ኮሚሽን በ13 አኙአክ ሰላማዊ ሰዎች ላይ በተፈፀመው ሕገ-ወጥ ግድያ የመከላከያ ሠራዊቱ

እንደነበረበት ማስረጃ አግኝቷል። ባልተረጋገጡ ዘገባዎች መሰረት አንድ የሞተባቸውን ወታደር መበቀል የፈለጉ ወታደሮች መጋቢት 20ቀን ስምንት አጅዋክ ሽማግሌዎችን በጮቦ መንደር ወዲያውኑ ረሽነዋል። (ክፍል 5ን ይመልከቱ)

ከቀደመው ዓመት ከደረሰው በሚለይ ሁኔታ በመንግሥት ታስረው ሳሉ በተፈጸመባቸው ማሰቃየት ስለሞቱ ሰዎች ምንም ዘገባዎች አልነበሩም።

በተለይ በኦሮሚያ እና በሱማሌ ክልሎች በፀጥታ ኃይሎች ሕገ-ወጥ ግድያዎች ስለመፈጸማቸው ዘገባዎች ቀጥለዋል። ለምሳሌ የካቲት 22ቀን አንድ የወረዳ ፖሊስ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረውን ዓለሙ ተስፋዬን በኦሮሚያ ክልል ጥቁር እንጭኒ ላይ የተማሪዎች ተቃውሞ በተደረገበት ጊዜ ተኩሶ ገድሎታል። በኦሮሚያ ክልል በነቀምቴ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የነበረችው ዓመለወርቅ ቡሊ በትምህርት ቤቷ በፖሊስ በተፈጸመባት ድብደባ የተነሳ ሞታለች። መንግሥት ግን የሞተችው በተፈጥሮ ምክንያቶች ነው ብሏል።

የመንግሥት ሠራዊት አባላት ሰላማዊ ሰዎችን አሳፍሮ በሚጓዝ ተሽከርካሪ ላይ የካቲት 7/96 ተኩስ ከፍተው አሥር ሰዎች መግደላቸውን የሶማሌ ክልል ሹማምንት ዘግበዋል። ይህ ሁኔታም የተፈፀመው ወታደራዊ ተሽከርካሪው በነዴ ከተማ ሰላማዊ ሰዎቹ ይጓዙበት ከነበረው ተሽከርካሪ ከተጋጨ በኋላ መሆኑም ተገልጿል ።

በ1995 ዓ.ም. በደረሱት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የታወቀ አዲስ ነገር የለም በፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንዳለ ስለሞተው አበራ ሄይ ፣ በነሐሴ ወር በአዲስ አበባ በፌደራል ፖሊስ አባላት ስለተገደሉት ሁለት ሰዎች ፣ የወታደር የደንብ ልብስ በለበሱ በአንድ የአዲስ አበባ ቡና ቤት በታህሥሥ ወር ስለተገደሉት አምስት ሰዎች የሚታወቅ አዲስ ነገር የለም። ፌዴራል ፖሊስ ግድያውን የፈፀመው ሰው ወታደር አንዳልነበር ሲገልጽ፣ የአእምሮ ቀውስ ያለበትና በዓመቱ መጨረሻ ላይም በቁጥጥር ሥር የነበረ መሆኑን አስታውቋል።

በ1994 ዓ.ም. በፀጥታ ኃይሎች መገደላቸው ስለተዘገበው ምንም ነገር አልተገኘም። የኦነግ እና የኦብነግ ታጣቂዎች በአገሪቱ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ብዙ ጊዜ ከመንግስት ኃይሎች ጋር ግጭት መፍጠራቸውን ቀጥለዋል። በዚሁም ጊዜ ቁጥራቸው ያልታወቀ ሰላማዊ ሰዎችና የመንግሥት ኃይሎች ለሞት ተዳርገዋል።

በዓመቱ መጨረሻ፣ ብዙዎቹ ከ1990 እስከ 1992 ዓ.ም. ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት ቅሪት የሆኑ፣ 2 ሚሊዮን ያህል ፈንጂዎች በአገሪቱ መሬት እንደተቀበሩ ነበር። የመንግሥት ፈንጂ አምካኝ ክፍል ፈንጂዎች በድንበር አካባቢ በመፈለግ እና በማምከን ረገድ በተወሰነ ደረጃ ወደፊት መግፋቱን ቀጥሏል። በኤርትራ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የተመድ የሰላም አስከባሪ ሹማምንት በኢትዮጵያ እና ኤርትራ የጋራ ድንበር በዓመቱ ውስጥ በሁለቱም በኩል አዳዲስ ፈንጂዎች የተቀበሩ መሆኑን ዘግበዋል።

ሚያዝያ 21/96 አንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው በትግርኛ ቋንቋ ፕሮግራም ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቴሌቪዥን ወደ ሚታይበት ክፍል የእጅ ቦምብ ወርውሮ አንድ ተማሪ በመግደል ሌሎች ስምንት ተማሪዎችን አቁስሏል። ከአደጋው ጋር በተያያዘ ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር ያዋለ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ ቀደም ብሎ በጥር ወር በተደረጉ ቅሬታ የማሰማት እርምጃዎች የተነሳ ታግደው የቆዩ ጥቂት የአ.አ. ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ይገኙበታል። (ክፍል 1 ሐን ይመልከቱ) ከአመቱ መጨረሻ ጀምሮ ተጠርጣሪዎች በዋስ የተፈቱ ቢሆንም፣ ጉዳዩ እንደተንጠለጠለ አለ።

ሚያዝያ 25/96 አንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ደብረዘይት፣ ኦሮሚያ ክልል ወደ እሚገኘው የአንድ ትግሬ ሴት ሱቅ ውስጥ የእጅ ቦምብ ወርውሮ አንድ ትግራዊ ዘመዷን ገድሏል። ፖሊስ ጥቃቱ በአነግ የሰነዘረ ነው ብሏል።

በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ሰገን ሆቴል ላይ በሐምሌ 1995 ዓ.ም. ቦምብ ተወርውሮ በ31 ሰዎች ላይ ስላደረሰው ጉዳት፣ ወይም በመስከረም 1995 ዓ.ም. አዲኳላ አቅራቢያ በመንገደኞች ባቡር ላይ ቦምብ ተወርውሮ ሁለት ሰዎችን በመግደል በዘጠኝ ሰዎች ላይ ስላደረሰው ጉዳት ምንም አዲስ ነገር አልተገኘም።

የንጣ ግጭቶች በዓመቱ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሞቶችን አድርሰዋል። (ክፍል 5 ን ይመልከቱ)

በአዲስ አበባ የሚገኘው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰዎችን ካለፍርድ መግደልን ጨምሮ የዘር ማጥፋትና ሌሎችንም የጦር ወንጀሎች ከ1967 እስከ 1983 በነበረው

የደርግ አገዛዝ ወቅት ፈጽማችኋል በማለት በይፋ የተከሰሱትን ወገኖች የክስ አፈጻፀም ሂደት ሲሰማ እና ሲከታተል ቆይቷል ። (ክፍል 1 ሠን ይመልከቱ)።

ለ/ መሰወር

በዓመቱ ውስጥ የመንግስት ኃይሎች ሰዎች እንዲሰወሩ ስለማድረጋቸው አንዳንድ ዘገባዎች የተደረጉ ሲሆን፣ ከተሰወሩት ውስጥ ጥቂቱ በፖለቲካ ምክንያት ሳይሆን አልቀረም። አብዛኛው የፀጥታ ኃይሎች ካለምንም የፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ አፍነው በመውሰድ ፣ ባልታወቁ ሥፍራዎች ከሳምንታት እስከ ወራት ለዘለቁ የተለያዩ ጊዜያት አግተዋቸዋል። ለምሳሌ በግንቦት ወር ውስጥ በሜጫ እና ቱለማ ማህበር (ሜቱማ) ታዋቂነት ያለው የኦሮሞ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ እና የባህል ድርጅት ፣ ዘበኛ የነበረውን ጅግሳ ሶሬሳን የፀጥታ ኃይሎች አፍነው ወስደዋል። ጂግሳ በዓመቱ መባቻ ላይ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት እንደታገተ መሆኑ ተዘግቧል።

የአፋር ክልላዊ መንግሥት የመረጃ /ኢንፎርሜሽን መኮንን የነበረው አህመድ ሃጂ ዋሴ በአፋር አማፂዎች እና በመንግሥት ወታደሮች ጦርነት ስለመኖሩ በመዘገቡ በታህሣሥ ወር 1996 ዓ.ም. ባልታወቀ ሥፍራ ታግቶ የት እንደሚገኝ እስካሁን ድረስ አዲስ መረጃ የለም።

በመስከረም 1995 አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው ትግራይ ሆቴል ላይ በተጣለው ቦምብ ምክንያት ታግተው የነበሩት መስፍን ኢታና፣ ይልማ ሞሲሳ እና ጋዲሳ ሞሲሳ መሰወራቸው ከታመነበት በኋላ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንደሚገኙ መንግሥት ዘግቧል (ክፍል 1 ሀ ን ይመልከቱ)። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ብዙ ወጣት ኦሮሞ ነጋዴዎች እንደተሰወሩ ናቸው።

በዓመቱ መጨረሻ ራያ አባ ሜጫ የሚባለው ኦሮሞ ድምፃዊ የት እንደሚገኝ አልታወቀም። ይህን ጉዳይ በሚመለከት በዓመቱ ውስጥ ምንም አዲስ መረጃ አልተገኘም።

መሰወራቸው ስለተዘገበው በርካታ ወጣት ኦሮሞ ነጋዴዎች በ 1995 ዓ.ም. መጨረሻ ምንም መረጃ አልነበረም።

በመጋቢት 1995 የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መሰወራቸውን ስለዘገበው 39 ሰዎች ምንም አዲስ መረጃ አልተገኘም።

በ1994 ዓ.ም. ከአንድ አውቶቡስ ላይ ታፍነው በኋላም በግፍ ስለ ተገደሉት 39 ኑዌር የአገር ውስጥ ተፈናቀዮች በ 1995 መንግሥት የማጣራት ምርመራ አካሂዷል። አራት የፖሊስ መኮንኖችን ጨምሮ አስር የክልል መንግሥት ሹማምንት በቁጥጥር ሥር ውለው ነበር። ባለፈው ዓመት መጨረሻ ይህ ጉዳይ እንደተንጠለጠለ ነበር።

ሐ/ ማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ ፣ ኢሰብዓዊ ፣ ወይም ሰውን የሚያዋርዱ አያያዞች ወይም ቅጣቶች

ሕገ መንግሥቱ ማሰቃየትን እና ማንገላታትን ይከለክላል። ሆኖም ፣ የፀጥታ ሹማምንት አዘውትረው ታጋቾችን እንደሚደበድቡ ወይም እንደሚያንገላቱ በዓመቱ ውስጥ የሚታመኑ ዘገባዎች በብዛት ነበሩ ። ደጋፊዎቻቸውን ብዙ ጊዜ እና በተቀናጀ ሁኔታ ፖሊስ እና የመንግሥት ታጣቂዎች የመብት ረገጣ እንደሚፈጽሙባቸው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘግበዋል ።

ቀደም ካለው ዓመት በተለየ ሁኔታ ባለፈው ዓመት ውስጥ ሞትን ያስከተለ ማሰቃየት ስለመፈጸሙ አንዳችም ዘገባዎች አልነበሩም።

የመንግሥት ታጣቂዎች የሚፈጽሙባቸው ጥቃት በዓመቱ ውስጥ መባባሱን የመኢአድ ደጋፊዎች ዘግበዋል። የአካባቢው ሹማምንት ብዙውን ጊዜ ጥቃቶቹን አይተው እንዳላዩ ይሆናሉ፣ ወይም በጥቃቶቹ ይተባባራሉ። ሚያዝያ 27/96 በሸበል በረንታ ወረዳ የሱሃ ተፋሰስ የገበሬዎች ማህበር አባል የሆነው ሃብታሙ ባዬ ከአንድ የመኢአድ ስብሰባ ሲመለስ የመንግሥት ታጣቂዎች ደብድበውታል። ሚያዝያ 28 ሀብቴ እንዳለ እና ቢምረው አዳል የተባሉ የመንግሥት ታጣቂዎች እንደሻው ዓለሙ የሚባለውን የመኢአድ ደጋፊ በእነማይ ወረዳ ምዕራብ ጎጃም ፣ አማራ ክልል ደብድበውታል። በመኢአድ ዘገባዎች መሰረት ግንቦት 5 የመንግሥት ታጣቂዎች የመኢአድ አደራጅ የሆነውን ዳምጠው አየለን በራቤል ወረዳ፣ ሰሜን ሸዋ ፣ አማራ ክልል ደብድበውታል። ድብደባው በፈጸሙት ወገኖች ላይ ምንም እርምጃ አልተወሰደም።